የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የተዘጋጀ

# በጋምቤላ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች ከግንቦት ወር 2015 ዓ.ም. ጀምሮ በተለያዩ ወቅቶች በተከሰቱ ግጭቶች እና የጸጥታ መደፍረስ ሁኔታዎች ሳቢያ የደረሱ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ የተደረገ የምርመራ ሪፖርት



የካቲት 2016 ዓ.ም.

www.ehrc.org

# ማውጫ

1. መግቢያ ........ 1
2. ዳራ ........ 2
3. የሕግ ማዕቀፍ ........ 2
4. የምርመራው ዋና ዋና ግኝቶች ........ 4
4.1. የሰዎች ሞትና እና የአካል ጉዳት ........ 4
4.2. በኢታንግ ልዩ ወረዳ የተለያዩ ቀበሌዎች የተከሰቱ ግጭቶች ........ 4
4.3. በጋምቤላ እና ጎግ ወረዳዎች የደረሱ ጥቃቶች ........ 7
4.4. ጋምቤላ ከተማ የደረሱ ጥቃቶች ........ 7
4.5. በስደተኞች ላይ የደረሰ ሞት እና አካል ጉዳት ........ 8
4.6. በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት እና ዘረፋ ........ 10
5. የመንግሥት አካላት ምላሽ ........ 11
6. ምክረ-ሐሳቦች ........ 13

# 1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ/ኮሚሽኑ) በጋምቤላ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች ከግንቦት ወር 2015 ዓ.ም. እስከ ሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. በተከሰቱ ግጭቶች እና የጸጥታ መደፍረስ ሁኔታዎች ዙሪያ ከመስከረም 20 እስከ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም. ድረስ በአካባቢው በመገኘት ምርመራ አድርጓል፡፡ እንዲሁም ከመስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም. በኋላ እስከ ጥር ወር 2016 ዓ.ም. ባለው ጊዜ በተለያዩ ወቅቶች የተከሰቱ ግጭቶችን እና ተያያዥ የመንግሥት እርምጃዎችን በተመለከተ ያሉ መረጃዎችን ክትትል በማድረግ በዚህ ሪፖርት ተካቷል፡፡ በዚህም መሠረት ኮሚሽኑ በጎግ ወረዳ፣ በጋምቤላ ወረዳ፣ በኢታንግ ልዩ ወረዳ አቼዋ ቀበሌ፣ ፒኖ ንኡስ ቀበሌ፣ እንዲሁም በቴምፒኝ መንደር እና በጋምቤላ ከተማ አስተዳደር የተለያዩ አካባቢዎች በአካል በመገኘት ከተጎጂዎች፣ ከተጎጂ ቤተሰቦች፣ ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከሃይማኖት መሪዎች እና ከዐይን ምስክሮች ጋር ቃለ መጠይቆችን እና የቡድን ውይይቶችን በማድረግ 93 ሰዎችን አነጋግሯል፡፡

በተጨማሪም በየደረጃው ከሚገኙ የተለያዩ የመንግሥት የአስተዳደር እና የጸጥታ አካላት ጋር ውይይቶች እና ቃለ-መጠይቆችን አከናውኗል፡፡ በዚህም ከጋምቤላ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን፣ ሰላም እና ጸጥታ ጉዳዮች ቢሮ፣ የክልሉ ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት፣ እንዲሁም ከአኝዋ እና ከኑዌር ብሔረሰብ ዞን አስተዳደር የሰላም እና ጸጥታ ቢሮዎች ጋር ውይይቶች ተደርገዋል፡፡ ኮሚሽኑ የጸጥታ ችግሮች በተከሰቱባቸው ወረዳዎች ደረጃ ከኢታንግ ልዩ ወረዳ አስተዳደር እና ከወረዳው የፖሊስ ጽሕፈት ቤት የወንጀል መከላከል ዘርፍ፣ ከላሬ ወረዳ ሰላምና ጸጥታ ጽሕፈት ቤት፣ ከጋምቤላ ወረዳ ፖሊስ ጽሕፈት ቤት፣ ከጎግ ወረዳ አስተዳደር እና ከወረዳው የሰላም እና ጸጥታ ጉዳዮች እና ፖሊስ ጽሕፈት ቤቶች ኃላፊዎች እና ተወካዮች ጋር ውይይቶች እና ቃለ-መጠይቆች አድርጓል፤ እንዲሁም ከጋምቤላ ከተማ አስተዳደር እና በከተማው ውስጥ ከሚገኙ ሁሉም የቀበሌ አስተዳደሮች መረጃዎችንና ማስረጃዎችን አሰባስቧል፡፡ በተጨማሪም ኮሚሽኑ ከስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት የጋምቤላ ቅርንጫፍ ቢሮ እና በተለያዩ ወረዳዎች ከሚገኙ የቢሮው የካምፕ አስተዳደር እና ከፌዴራል ፖሊስ የወንጀል መከላከል ደቡብ ምዕራብ መምሪያ የሬጅመንት ሁለት ጋምቤላ ጽሕፈት ቤት መረጃዎችን እና ምላሾችን ተቀብሏል፡፡ የጸጥታ ችግር ተከስቶባቸው በነበሩ እና ተደራሽ በሆኑ ሥፍራዎች ኮሚሽኑ በአካል ምልከታ አድርጓል፤ የፎቶግራፍ እና የተንቀሳቃሽ ምስሎች ማስረጃዎችንም አሰባስቧል፡፡

ኢሰመኮ ምርመራውን ያካሄደው አግባብነት ያላቸው ዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ እና ሀገራዊ የሕግ ማዕቀፎችን መሠረት በማድረግ ሲሆን፣ በተሰበሰቡ መረጃዎች እና ማስረጃዎች መነሻነት ግኝቶች ወይም ድምዳሜዎች ላይ ለመድረስ ተግባር ላይ የዋለው በተመሳሳይ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ምርመራ ላይ ተግባራዊ የሚደረገው "ምክንያታዊ አሳማኝነት" (reasonable grounds to believe) የማስረጃ ምዘና ደረጃ/ስልት ነው፡፡ በዚህም መሠረት ኮሚሽኑ የአንድ ጥሰት መፈጸም ወይም አለመፈጸምን አስመልክቶ ድምዳሜ ላይ የሚደርሰው ጉዳዩን አስመልክቶ ከተለያዩ ተዓማኒነት ካላቸው ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎች እርስ በርስ ተመሳሳይነት ያለው ወይም የማይጣረስ መረጃ መስጠታቸውን እና አንድ ምክንያታዊ የሆነን ሰው ሊያሳምን በሚችል አግባብ ስለ አንድ ነጠላ ክስተት ወይም ስልትና አሠራርን የሚያሳይ ተደጋጋሚ ጥሰትን (አዝማሚያ/pattern) የሚያስረዳ ሲሆን ነው፡፡

## 2. ዳራ

የጋምቤላ ክልል ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ክልሎች ውስጥ አንዱ ሲሆን፣ የቆዳ ስፋቱ 25,369 ካሬ ኪ.ሜ. ሆኖ በሰሜን ምሥራቅ ከኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ምሥራቅ ከደቡብ ምዕራብ ክልል እና በምዕራብ ከደቡብ ሱዳን ጋር የሚዋሰን ነው፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት መረጃ በሰኔ ወር 2015 ዓ.ም. የጋምቤላ ክልል ሕዝብ ብዛት በአጠቃላይ 525,000 (አምስት መቶ ሃያ አምስት ሺህ) እንደሚሆን እና ከዚህም ውስጥ 273,000 (ሁለት መቶ ሰባ ሶስት ሺህ) ወይም 52% ያህሉ ወንዶች መሆናቸውን እና 252,000 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ) ወይም 48% ያህሉ ሴቶች እንደሆኑ ያሳያል፡፡

የጋምቤላ ክልል ከደቡብ ሱዳን የመጡ ከ384,000 በላይ የሚሆኑ ስደተኞችን ተቀብሎ ቴርኪዲ፣ ኩሌ፣ ጀዌ፣ ፑኚዶ አንድ እና ሁለት፣ ዊኜል እና ኦኩጎ በተባሉ

የስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎች የሚያስተናግድ ነው፡፡

በክልሉ በተለያዩ ጊዜያት ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በአኝዋ እና ኑዌር ብሔረሰብ አባሎች መካከል ግጭቶች ተከስተዋል፡፡ እነዚህ ግጭቶች የተለያዩ መንስኤዎች የነበራቸው ቢሆንም በዋናነት ከተፈጥሮ ሀብት (Resources) አጠቃቀም፣ እንዲሁም ከማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ጉዳዮች ጋር የተያየዙ ነበሩ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በክልሉ የስደተኞች ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ ከተቀባይ ማኅበረሰብ የሚነሱ ቅሬታዎች የግጭት ምክንያቶች እየሆኑ መጥተዋል፡፡ አብዛኛዎቹ የታጠቁ ቡድኖች አደረጃጀቶች ብሄረሰባዊ ጠባይ ያላቸው ሲሆን፤ በእነዚህ ታጣቂ ቡድኖች የሚፈጸሙ ጥቃቶችም ብሔረሰባዊ ትኩረት ወይም አዝማሚያ ይታይባቸዋል፡፡

## 3. የሕግ ማዕቀፍ

ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች[1] ያለምንም አድሏዊ ልዩነት በግዛቷ ውስጥ ሰብአዊ መብቶችን የማክበር፣ የማስከበር እና የማሟላት ግዴታዎች እንዳሉባት ይደነግጋሉ፡፡ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን መመርመር፣ የአጥፊዎችን ተጠያቂነት ማረጋገጥ እና ለተጎጂዎች በቂ እና ውጤታማ የሆነ መፍትሔ መስጠት ከእነዚህ ግዴታዎች መካከል ይገኙበታል፡፡ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 13 (2) ላይ በሕገ መንግሥቱ ምዕራፍ ሦስት ዕውቅና ተሰጥቷቸው የተዘረዘሩ መሠረታዊ የመብቶች እና የነጻነት ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች እና ዓለም አቀፍ ሰነዶች መርሖዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ እንደሚተረጐሙ ይደነግጋል፡፡

በሕይወት የመኖር መብት በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 3፣ በዓለም አቀፍ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ቃልኪዳን አንቀጽ 6፣ በአፍሪካ የሰዎች እና ሕዝቦች መብቶች

[1] ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከወጡ ዘጠኝ (9) ዋና ዋና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች ውስጥ የሰባቱ (7) አባል ሀገር ነች፡፡ እነዚህም፡- አድሎአዊ የዘር ልዩነቶችን ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት፣ በሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውንም አድሎአዊ ልዩነት ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት፣ የሕፃናት መብቶች ስምምነት፣ ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት፣ የማሰቃየት እና ሌሎች የጭካኔ፣ ኢ-ሰብአዊ የሆነና ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት ለማስቀረት የተደረገ ስምምነት፣ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን፣ እንዲሁም የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ እና የባህል መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳን ናቸው፡፡

ቻርተር አንቀጽ 4፣ በሁሉን አቀፍ/ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 3፤ እንዲሁም በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 15 ላይ በከፍተኛ ደረጃ ጥበቃ የተደረገለት መብት ነው። በተያያዘም የአካል ደኅንነት መብት በዓለም አቀፍ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ቃልኪዳን በአንቀጽ 9 ላይ ጥበቃ የተደረገላቸው ሲሆን፤ በተመሳሳይ ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት፣ እንዲሁም የማይደፈርና የማይገሰስ የአካል ደኅንነትና ነጻነት መብት እንዳለው የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 16 ደንግጓል። የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ማንም ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት በማንኛውም ዐይነት መሣሪያ ወይም ዘዴ ሌላውን ሰው የገደለ ወይም አካል ያጎደለ ወይም ጤንነቱን የጐዳ እንደሆነ በወንጀል እንደሚቀጣ አንቀጽ 538-544 እና 553 ይደነግጋል።

የንብረት መብት በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 17፣ በአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 14፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 40 ላይ ዕውቅና ያገኘ እና ጥበቃ የሚደረግለት መብት ነው።

በነጻነት የመንቀሳቀስ መብት በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 13፤ በዓለም አቀፍ የሲቪል እና ፖለቲካ መብቶች ቃልኪዳን በአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 12(1)፤ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 32 ላይ ጥበቃ የተደረገለት መብት ነው።

ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. በ1951 ከስደተኞች ሁኔታ ጋር በተያያዘ የተደረሰው ስምምነት እና እ.ኤ.አ. በ1967 የወጣው ፕሮቶኮል፤ እንዲሁም በ1951 የተደረገው ስምምነት "የስደተኞችን ሁኔታ በተመለከተ መሠረታዊው እና ዓለም አቀፉ ሕጋዊ ሰነድ" እንደሆነ የሚያረጋግጠውና አፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ስደተኞች ዝርዝር ጉዳዮችን ለማስተዳደር በአፍሪካ አንድነት ድርጅት እ.ኤ.አ. 1969 የወጣው ስምምነት ፈራሚ ሀገር ነች። በ1951 የወጣው ስምምነት አንቀጽ 1 መሰረት "ስደተኛ" ማለት ማንኛውም "በዘሩ፣ በሃይማኖቱ፣ በብሔሩ፣ በአንድ የተለየ ማኅበራዊ ቡድን አባልነቱ ወይም በፖለቲካ አስተያየቱ ምክንያት እንደሚሳደድ ብርቱ መሠረት ያለው ፍርሃት አድሮበት ከዜግነት ሀገሩ ውጪ የሚገኝ እና በዚሁ ፍርሃት ምክንያት የዚያን ሀገር ጥበቃ መሻት የማይችል ወይም የማይፈልግ፣ ወይም ዜግነት የሌለው በመሆኑ እና ከዚህ በፊት መኖር ከለመደበት ሀገር በዚሁ ምክንያት የወጣ፣ በዚሁ ፍርሃት ምክንያት ወደዚያ ሀገር መመለስ የማይችል ወይም የማይፈልግ ሰው ማለት ነው።

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ስምምነት በ1951 በወጣው ስምምነት ውስጥ ያለውን የስደተኛ ትርጓሜ በማስፋት የትውልድ ወይም የዜግነት ሀገሩ በውጪ ኃይል በመወረሩ፣ በመያዙ፣ በውጪ ኃይል ቁጥጥር ሥር በመሆኑ ወይም ሙሉ ሀገሩን ወይም የሀገሩን አንዱን ክፍል ሰላምና መረጋጋት ሥርዓት በእጅጉ የሚረብሹ ክስተቶች በመፈጠራቸው ምክንያት መኖር የለመደበትን ሀገር ጥሎ ለመሰደድና በሌላ ቦታ መጠለያ ለመፈለግ የተገደደ ማንኛውም ሰው ነው የሚለውን ሰፋ ያለ ትርጓሜ እንዲያካትት አድርጓል።

ኢትዮጵያ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ስምምነቶች ፈራሚ ሀገር እንደመሆኗ፤ በሥልጣን ግዛቷ ወሰን ውስጥ የሚገኙ ስደተኞችን ደኅንነት የመጠበቅ ግዴታ አለባት። በተጨማሪም በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ግዴታዎች መሠረት፤ ለስደተኞች አግባብነት ያላቸውን መብቶች የማክበርና የማረጋገጥ፣ እንዲሁም መንግሥት በዚህ ረገድ ልዩ ልዩ ተግባራቱን በሚፈጽምበት ወቅት ከተባበሩት መንግሥታት ከፍተኛ የስደተኞች ኮሚሽነር ጋር

የመተባበር እና በ1951 የተደረገውን ስምምነት አፈጻጸም የመቆጣጠር ኃላፊነቱን እንዲወጣ የማመቻቸት ግዴታም አለበት፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና ለተሰጣቸው የስደተኞች መብቶች በኢትዮጵያ ደረጃም ዕውቅና የመስጠት እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር በስደተኞች መብቶች አጠባበቅ ዙሪያ ለሚያከናውናቸው ሥራዎች ትብብር የማድረግ ግዴታዎችን ይጨምራል፡፡

በኢትዮጵያ የስደተኞችን መብቶች በተሻለ ሁኔታ ለመጠበቅ እና ለስደተኞች ዘላቂ መፍትሔዎችን ለማፈላለግ የሚያስችል ዓለም አቀፍ መመዘኛዎችን መሠረት ያደረገ የሕግ ማዕቀፍ ለመፍጠር የሚያስችል የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1110/2011 በኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጸድቋል፡፡ በዚህ አዋጅ ከተካተቱ የስደተኞች መብቶች መካከል ስደተኛ በመረጠው የሀገሪቷ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመሥረት፣ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ የመሆን፣ ንብረትን በባለቤትነት የመያዝ እና ከጥቃት፣ ከብዝበዛ እና ከእንግልት የመጠበቅ እንዲሁም ፍትሕ የማግኘት መብቶችን ይጨምራል፡፡

አዋጁ በስደተኞችም ላይ ግዴታዎችን ያካተተ ሲሆን ማንኛውም ስደተኛ እና ጥገኝነት ጠያቂ በኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ባሉ በማናቸውም ሕጎች እና ድንጋጌዎች እንደሚገዛ፣ የሚኖርበትን አካባቢ ባህል የማክበር እና ከአካባቢው የመልካም አኗኗር እና የሕዝብ ሞራል ተቃራኒ ከሆኑ ተግባራት የመቆጠብ ግዴታ እንዲሁም አካባቢውን የመንከባከብ ኃላፊነት እንዳለበት/ባት ይደነግጋል፡፡

# 4. የምርመራው ዋና ዋና ግኝቶች

## 4.1. የሰዎች ሞትና እና የአካል ጉዳት

በጋምቤላ ክልል፣ ኢታንግ ልዩ ወረዳ የተለያዩ ቀበሌዎች ውስጥ፣ በጋምቤላና በጎግ ወረዳዎች እንዲሁም በጋምቤላ ከተማ ውስጥ ከግንቦት ወር 2015 ዓ.ም. ጀምሮ በነበሩ ግጭቶች የተነሳ በክልሉ የሚኖሩ ስደተኞችን ጨምሮ ቢያንስ 138 ሰዎች መገደላቸውን፣ 113 ሰዎች ላይ ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት መድረሱን፣ ነዋሪዎች መፈናቀላቸውን፣ በርካታ ቤቶች፣ ንብረቶች መቃጠላቸውን እና ዘረፋ መፈጸሙን ኮሚሽኑ ካሰባሰባቸው መረጃዎች እና ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 4.2. በኢታንግ ልዩ ወረዳ የተለያዩ ቀበሌዎች የተከሰቱ ግጭቶች

ከግንቦት ወር 2015 ዓ.ም. ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ወራት በኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ፒኝዋ ቀበሌ ነዋሪ የነበረ ሰው ግንቦት 13 ቀን 2015 ዓ.ም. ጫካ ለእንጨት ለቀማ ሄዶ መጥፋቱን ተከትሎ፣ በፒኝዋ እና ሌር ቀበሌ ነዋሪዎች መካከል የተፈጠረው አለመግባባት ቀስ በቀስ ወደ ማኅበረሰባዊ ግጭት (Inter-communal conflict) በመሸጋገር በደረሱ ጥቃቶች የተነሳ ቢያንስ 82 ሰዎች ሕይወታቸው አልፏል፤ እንዲሁም ወደ 80 የሚሆኑ ሰዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡

ሐምሌ 5 ቀን 2015 ዓ.ም. ከቀኑ 6:00 ሰዓት አካባቢ በፑኩሙ ቀበሌ አኛሊ መንደር ወፍጮ ቤት ውስጥ የታጠቁ ቡድኖች ድንገት በከፈቱት ተኩስ አንድ ሕፃን ልጅ በጥይት ከተመታች በኋላ

ለህክምና ወደ ሆስፒታል ተወስዳ ከ5 ቀናት በኋላ ሕይወቷ ማለፉን እና ሁለት ሴቶች በተተኮሰባቸው ጥይት መቁሰላቸውን ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው የሟች ቤተሰብ እና ምስክሮች አስረድተዋል፡፡

ሐምሌ 13 ቀን 2015 ዓ.ም. ከቀኑ 5፡00 ሰዓት አካባቢ በፒኖ ቀበሌ ላይ በሌር እና ፒኖ ቀበሌ ነዋሪዎች መካከል በተከሰተ የእርስ በእርስ ግጭት ቢያንስ የ46 ሰዎች ሕይወት ማለፉን፤ 46 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት መድረሱን እና ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ነዋሪዎች መፈናቀላቸውን ኮሚሽኑ የተጎጂ ቤተሰቦችን፣ የዐይን ምስክሮችን፣ የአካባቢውን ነዋሪዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎችን፤ የቀበሌ አመራሮችን እና የወረዳ አስተዳዳሪዎች በማነጋገር ለማወቅ ችሏል፡፡

በሐምሌ 13 ቀን 2015 ዓ.ም. በፒኖ ቀበሌ በተከሰተው ግጭት በቦታው የነበሩ የፒኖ ነዋሪዎች ለኮሚሽኑ ሲያስረዱ፡-

> *"በኢታንግ ልዩ ወረዳ አኩራ ቀበሌ፣ ፒኖ ንኡስ ቀበሌ ሐምሌ 13 ቀን 2015 ዓ.ም. ከቀኑ 5፡00 ሰዓት አካባቢ ቁጥራቸው በዛ ያለ የታጠቁ [ሰዎች] እንደ ብሬን ዐይነት ከባድ የጦር መሣሪያ ታጥቀው በመምጣት በርካታ ሰዎችን በጥይት ገድለው፣ በርካታ ሰዎችን አቆሰሉ፡፡ ወደ 5 የሚሆኑ ሰዎች ከጥቃቱ ለማምለጥ ሲሞክሩ ባሮ ወንዝ ውስጥ ገብተው ቀሩ፡፡ ጥቃት ከተፈጸመባቸው ሰዎች መካከል ሕፃናት እና ሴቶች አሉበት፡፡ በጥቃቱ ወደ 58 የሚሆኑ የሳር ቤቶች ተቃጥለዋል፡፡ ወቅቱ እኛ ቤት አካባቢ ሥራ ላይ ነበርን፡፡ ሊያጠቁን የቻሉት በምን ምክንያት እንደሆነ እስካሁን አልገባንም፡፡"* በማለት ለኮሚሽኑ አስረድተዋል፡፡

በተመሳሳይ ሐምሌ 13 ቀን 2015 ዓ.ም. በፑኩሙ ቀበሌ ውስጥ በታጠቁ ቡድኖች አንድ ሰው በጥይት እንደተገደለ ኮሚሽኑ ካነጋገራቸው ምስክሮች ለማወቅ ችሏል፡፡

በሐምሌ 18 ቀን 2015 ዓ.ም. ከሌሊቱ 10፡00 ሰዓት ጀምሮ የታጠቁ ቡድኖች በሌር ቀበሌ ላይ በፈጸሙት ጥቃት ቢያንስ የ19 ሰዎች ሕይወት ማለፉን እና 11 ሰዎች መቁሰላቸውን ኮሚሽኑ ከምስክሮች፣ ከተጎጂዎች፣ ከተጎጂ ቤተሰቦች፣ ከነዋሪዎች እና ከመንግሥት አካላት ባሰባሰበው መረጃ እና ማስረጃ አረጋግጧል፡፡

ኮሚሽኑ በቡድን ውይይት ያነጋገራቸው የሌር ቀበሌ ነዋሪዎች ስለግጭቱ መነሻ፤ በሐምሌ 13 እና 18 ቀን 2015 ዓ.ም. እና በሌሎች ቀናቶች የደረሱት ግጭቶች ስላስከተሉት ጉዳት እንደሚከተለው አስረድተዋል፡-

> *"ግንቦት 13 ቀን 2015 ዓ.ም. አንድ የአካባቢው ነዋሪ እንጨት ለመልቀም ወደ ጫካ በሄደበት ጊዜ ከባድ ዝናብ ጥሎ ግለሰቡ ሳይመለስ በመቅረቱ የፒኙዋ ቀበሌ ነዋሪዎች ወደእኛ ቀበሌ መጥተው ሰውዬውን የገደላችሁት እናንተ ናችሁ አሉን፣ እኛም የጠፋውን ሰው ጡሩምባ ነፍታችሁ ፈልጉ ብለን ምላሽ ሰጠናቸው፡፡ ከዚያም ጡሩምባ ተነፍቶ ሰውየው ቢፈለግም ማግኘት አልተቻለም፡፡ በዚህ የተነሳ በፒኙዋ እና ሌር ቀበሌዎች ነዋሪዎች መካከል አለመግባባት ሲፈጠር ጉዳዩ ወደ ኢታንግ ልዩ ወረዳ አስተዳዳሪ ደርሶ የወረዳው አስተዳዳሪ ወደ ኢታንግ ከተማ እንድንመጣ ባዘዘን መሠረት 20 ሰዎች ሁነን ሄድን፤ ነገር ግን የፒኙዋ ቀበሌ አመራሮች ስላልቀረቡ ለሦስት ቀናት በመጉላላታችን እና ከተማ ላይም እየተቸገርን በመሆኑ ከዚህ በላይ መጠበቅ እንደማንችል ለወረዳው አሳውቀን ወደ ሌር ቀበሌ በመመለስ ላይ ሳለን መኮድ መንገድ ላይ ተኩስ ተከፈተብን፡፡ ለአስተዳዳሪው*

*ወዲያው በመደወል ተኩስ እንደተከፈተብን ስንነግረው እነማናቸው ሲለን የእኛን ጥርጣሬና ግምት ነገርነው፡፡ እንዴት አወቃችሁ ብሎ ሲጠይቀን አንተ የበላይ ኃላፊ ስለሆንክ ፖሊስ ላክና ጉዳዩ እንዲጣራ አድርግ፤ እኛም የሄዱበትን መንገድ እናሳያቸዋለን ብለን መለስንለት፡፡ ከዚያ በኋላ የፒኝዋ ቀበሌ ነዋሪዎች ሥጋት አለብን፤ ፖሊሶች ወደ ቀበሌው ተላኩ፡፡ የተላኩት ፖሊሶች ፒኝዋ ቀበሌ እንደደረሱ የቀበሌው ወጣቶች ወደ ሌር ቀበሌ በመምጣት ተኩስ ከፍተው 2 ሰው አቆሰሉ፣ የቆሰሉትን ለማንሳት ስንሄድ ፖሊሶች ከወጣቶቹ ጋር ተቀላቅለው ወደ እኛ በመተኮስ 2 ሰው ገድለው 4 ሰዎችን አቆሰሉብን፡፡ ይህ ከተፈጠረ ከሁለተኛው ቀን በኋላ የመንግሥት አካላት መጥተው አነጋግረውን ጉዳዩ ይጣራል፣ ተረጋግታችሁ ወደ ሥራችሁ ተመለሱ ተባልን፡፡ ከዛ እንጨት ለቀማ የሄዱ 2 ነፍሰጡሮች በጥይት ተመትተው ተገደሉ፡፡ ከመከላከያ ሰራዊት ጋር በመሆን አስከሬኑን አንስተን ቀበርን፡፡ በድርጊቱ ተናደን ወደ ፒኙዋ ተሰባስበን ስንሄድ መከላከያ ሰራዊት መለሰን፡፡ በሌላ ቀን ልጆቻችን በቆሎ ለማምጣት ወደ ባሮ ዳር ሲሄዱ በተከፈተባቸው ተኩስ ሁለቱ ቆሰለው ሌሎች ሮጠው አመለጡ፡፡ ነገሮች ተረጋግተው ወደ መደበኛ የእርሻ ሥራችን ተመልሰን እያለ ሐምሌ ወር ውስጥ የሌላ ቀበሌ ነዋሪዎች ጥቃት ከፈቱብን፡፡ እንደሚያጠቁን ስለምናውቅ ተዘጋጅተን ስለነበር ተከላክለን መለስናቸው፡፡ ከእርሻ ሥራችን እያባረሩ ሲያስቸግሩን የእኛም ልጆች በየቦታው እየተገደሉ ሲበዛብን ተሰባስበን ለመዋጋት ወደ ፒኖ ቀበሌ ሐምሌ 13 ቀን 2015 ዓ.ም. ሄድን፤ በእዚህ ቀን ግጭት የእኛ የሌር ቀበሌ ነዋሪ የሆኑ 14 ሰዎች ሕይወታቸው ሲያልፍ ሌሎች 12 ሰዎች ከቀላል እስከ ከባድ የሚሆን ጉዳት ደረሰባቸው፡፡ ከቀናት በኋላ ሐምሌ 18 ቀን 2015 ዓ.ም. ከለሊቱ 10፡00 ሰዓት ጀምሮ የታጠቁ ሰዎች ሌር ቀበሌ ድረስ መጥተው በከባድ መሣሪያ የታገዘ ጥቃት በመክፈት 2 ሴቶችና 6 ወንዶች/አረጋውያን ጎጆ ቤት ውስጥ እያሉ አቃጥለው ከገደሉ በኋላ 11 ሰዎችን በጥይት ገድለው 11 ሰዎችን አቆሰሉ፤ እንዲሁም ብዙ የሣር ቤቶች አቃጥለዋል፡፡"*

በእነዚህ ሁለት ቀበሌዎች በሚኖሩ ነዋሪዎች መካከል ከግንቦት ወር 2015 ዓ.ም. በፊትም አልፎ አልፎ በነበረ የእርስ በእርስ ግጭቶች ሰዎች በተለያየ ጊዜ እንደተገደሉ እና የአካል ጉዳት እንደደረሰባቸው የሚያስረዱ ነዋሪዎች እና ምስክሮችም አሉ፡፡ ለአብነት ያህል በሚያዝያ ወር 2015 ዓ.ም. ትክክለኛ ቀኑ ባልታወቀ ነገር ግን ሰዓቱ ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት አካባቢ በኢታንግ ልዩ ወረዳ አቹዋ ቀበሌ ቲዬሉል ሰፈር ውስጥ አንዲት ነፍሰጡር መሣሪያ በታጠቀ ግለሰብ በጥይት ተመትታ እንደተገደለች ነዋሪዎች እና ምስክሮች ለኮሚሽኑ አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም ከግንቦት 13 ቀን 2015 ዓ.ም. በኋላ በነበረው ግጭት ትክክለኛ ቀኖቹ ባልታወቀበት ነገር ግን በግንቦት እና ሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. ውስጥ በተለያየ ጊዜ ሰዎች ተግደለዋል፤ እንዲሁም የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡ በሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. በኢታንግ ልዩ ወረዳ በአንጎዬ እርሻ እና አከዶ መንገድ አካባቢ በታጠቁ ቡድኖች 11 ሰዎች መገደላቸውን የተጎዱ ቤተሰቦች፣ ነዋሪዎች እና ምስክሮች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም በሌር ቀበሌ ውስጥ በታጠቁ ቡድኖች በተፈጸመ ጥቃት 4 ሰዎች መገደላቸውን እና 8 ሰዎች መቁሰላቸውን ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው ነዋሪዎች፣ ምስክሮች እና የቀበሌው አመራሮች ገልጸዋል፡፡

በጥር 13 ቀን 2016 ዓ.ም. ከቀኑ 11፡00 አካባቢ ከኢታንግ ልዩ ወረዳ ተርፋም ቀበሌ ወደ ጋምቤላ ከተማ በመጓዝ ላይ በነበረ የህዝብ ማመላለሻ መኪና አካዶ ኬላ አካባቢ ሲደርስ ማንነታቸው ያልታወቁ የታጠቁ ሰዎች በግራ እና በቀኝ ድንገተኛ ተኩስ በመክፈት ከተሳፋሪዎች መካከል 15

በሚደርሱ ሰዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ ጉዳት ያደረሱ መሆኑን ኮሚሽኑ ተጎጂዎችን፣ የተጎጂ ቤተሰቦችን፣ ህክምና ሲያገኙ የነበሩበትን ሆስፒታል አስተዳደር እና የህክምና ባለሞያዎችን በማነጋገር ማወቅ ችሏል። በዚህ ጥቃት የተጠረጠሩ 2 ሰዎች በቁጥጥር ሥር እንደዋሉ እና ተጨማሪ ክትትል በማድረግ የቀሩትን ተጠርጣሪዎች በሕግ ቁጥጥር ሥር ለማዋል ጥረት እየተደረገ መሆኑን የጋምቤላ ክልል ሰላም እና ጸጥታ ጉዳዮች ቢሮ እና የጋምቤላ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ለኢሰመኮ ገልጸዋል።

### 4.3. በጋምቤላ እና ጎግ ወረዳዎች የደረሱ ጥቃቶች

ሰኔ 9 ቀን 2015 ዓ.ም. ከጠዋቱ 1:00 ሰዓት አካባቢ በጋምቤላ ወረዳ ከኡፓኛ ቀበሌ ወደ አቦል ከተማ በመንዝ ላይ የነበረ አንድ ተጎጂ የታጠቁ ሰዎች መሣሪያ ተኩሰው ጉዳት ካደረሱበት በኋላ ማምለጡን ለኮሚሽኑ አስረድቷል።

ሰኔ 10 ቀን 2015 ዓ.ም. ከቀኑ 10:00 ሰዓት ገደማ በጎግ ወረዳ እንጨት በመሸጥ ሲተዳደሩ የነበሩ ሁለት ሰዎች ወደ ጫካ እንጨት ለቀማ ሄደው በአህያ ጋሪ እንጨት ጭነው በሚመለሱበት ጊዜ ማንነታቸው ባልታወቀ ሰዎች እጃቸውን ወደ ኋላ በገመድ ታስረው በጥይት ተደብድበው ተገድለው መገኘታቸውን የሟቾች ቤተሰቦች እና የወረዳው አስተዳደር ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

ሰኔ 15 ቀን 2015 ዓ.ም. ከቀኑ 10:00 ሰዓት አካባቢ "የካርተር ሴንተር ኢትዮጵያ አቦቦ ከተማ ሠራተኛ" መሆኑ የተነገረ አንድ ሰው ቤተሰቡን ለመጠየቅ ፑኝዶ ከተማ ቆይቶ ወደ አቦቦ ከተማ በካርተር ሴንተር መኪና ጉዞ ላይ እያለ የፑኝዶ 2 የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ መግቢያ አካባቢ ሲደርስ በርካታ ስደተኞች የሆኑ ሰዎች ሟችን ከመኪናው በማውረድ በጦር በተደጋጋሚ በመውጋት ሕይወቱ እንዲያልፍ ያደረጉ መሆኑን የሟች የሥራ ባልደረቦች እና የወረዳው አስተዳደር አስረድተዋል።

በጋምቤላ ወረዳ እናት ጡት ተራራ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ ሰኔ 27 ቀን 2015 ዓ.ም. ለሊት አንድ ሰው ማንነታቸው ባልታወቀ ሰዎች በስለት ተወግቶ የተገደለ መሆኑን ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው የሟች ቤተሰቦች ገልጸዋል።

ነሐሴ 28 ቀን 2015 ዓ.ም. ከጠዋቱ 12:20 ሰዓት አካባቢ በጋምቤላ ወረዳ፣ ከኡፓኛ ቀበሌ ወደ አቦል ከተማ በተለምዶ ባጃጅ እየተባለ በሚጠራው ባለ ሦስት እግር ተሽከርካሪ ተሳፍረው እየሄዱ የነበሩ አራት ሰዎች ላይ በተተኮሰባቸው ጥይት ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ኮሚሽኑ ተጎጂዎችን በማነጋገር እና የደረሰባቸውን ጉዳት በመመልከት ማወቅ ችሏል።

### 4.4. ጋምቤላ ከተማ የደረሱ ጥቃቶች

ግንቦት 14 ቀን 2015 ዓ.ም. ከቀኑ 9:00 ሰዓት ገደማ በጋምቤላ ከተማ፣ 04 ቀበሌ ብሔር ብሔረሰብ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ አንድ ሰው እና ሐምሌ ወር 2015 ዓ.ም. ትክክለኛ ቀኑ ባልታወቀበት ነገር ግን ሰዓቱ ከቀኑ 10:00 ሰዓት አካባቢ ዶምቦስኮ ትምህርት ቤት አካባቢ አንድ ሰው ማንነታቸው ባልታወቀ የታጠቁ ሰዎች መገደላቸውን የተጎጂ ቤተሰቦች አስረድተዋል። በተመሳሳይ ጊዜ ከምሽቱ 12:00 ሰዓት አካባቢ በጋምቤላ ከተማ፣ 01 ቀበሌ ጀጀቤ ወንዝ አካባቢ 2 ሰዎች ማንነታቸው ባልታወቀ ሰዎች በጥይት ተመትተው መሞታቸውን የሟች ቤተሰቦች እና ምስክሮች ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

በጋምቤላ ከተማ 01 ቀበሌ ጀጀቤ ተራራ አካባቢ ሰኔ 24 ቀን 2015 ዓ.ም. ከቀኑ 11፡00 ሰዓት ገደማ 7 ሰዎች በጥይት የተገደሉ ሲሆን፤ ሰኔ 25 ቀን 2015 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት አካባቢ አንድ በአካባቢው ማኅበረሰብ የአእምሮ ሕመም እንዳለበት የተገለጸ ሰው በጋምቤላ ከተማ፣ 04 ቀበሌ የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ አካባቢ በቡድን በተሰባሰቡ ወጣቶች ጥቃት በስለት ተወግቶ መገደሉን ኮሚሽኑ የሟች ቤተሰቦችን እና ምስክሮችን በማነጋገር ለማወቅ ችሏል።

በተመሳሳይ ሰኔ 24 ቀን 2015 ዓ.ም. ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ገደማ በጋምቤላ ከተማ፣ 04 ቀበሌ ብሔር ብሔረሰብ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ቁጥራቸው ከ200 በላይ የሚሆኑ የቀድሞውን የጋምቤላ ክልል ልዩ ኃይል፣ የጋምቤላ ክልል መደበኛ ፖሊስ እንዲሁም የጋምቤላ ክልል ሚሊሻ መለዮ ልብሶችን የለበሱ እና ሌሎች የታጠቁ ሰዎች በሦስት የተለያየ አቅጣጫ በመግባት በቦታው የነበሩ ዘጠኝ ሰዎችን በጥይት መግደላቸውን እና ሌሎች አራት ሰዎች ላይ ጉዳት ማድረሳቸውን የዐይን ምስክሮች እና የተጎጂ ቤተሰቦች አስረድተዋል።

ሐምሌ 14 ቀን 2015 ዓ.ም. ከንጋቱ 11፡00 ሰዓት አካባቢ በጋምቤላ ከተማ፣ 04 ቀበሌ፣ ቁራ ሰፈር አጉኛ አካባቢ የታጠቁ ሰዎች ወደ አንድ መኖሪያ ቤት በመግባት ተኩስ ከፍተው፣ አንድ ሰው ሲገድሉ በሌላ አንድ ሰው ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳት አድርሰዋል። በዚህም የተነሳ ጉዳት የደረሰበት ቤተሰብ አባላት ከሚኖሩበት አካባቢ በሥጋት ለቀው ወደ ሌላ አካባቢ በመሄዳቸው ለከፍተኛ ችግር መዳረጋቸውን ለማወቅ ተችሏል።

በዚህ ጉዳይ ላይ የጥቃቱ ሰለባ የሆኑ አንድ ተጎጂ ስለነበረው ሁኔታ ሲያስረዱ፡-

> *"በጋምቤላ ከተማ፣ 04 ቀበሌ፣ ቁራ ሰፈር አጉኛ በሚባል ስፍራ በመኖሪያ ቤታችን ተኝተን ባለንበት ሰዓት ከንጋቱ 11፡00 ሰዓት ገደማ አምስት የሚሆኑ መሣሪያ የታጠቁ ሰዎች ቤታችንን ሰብረው በመግባት በተኛንበት ተኩስ ከከፈቱብን በኋላ ባለቤቴ ወዲያውኑ ሲሞት እኔ የግራ እጄ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶብኝ ወደ ሕክምና ከተወሰድኩኝ በኋላ የግራ እጄ ተቆርጦ አካል ጉዳተኛ ሆኛለሁ፤ በነበረው የጸጥታ ችግር የተነሳ በሥጋት ተፈናቅዬ የምገኝ ቢሆንም የተደረገልኝ ድጋፍ ባለመኖሩ ለከፍተኛ ችግር ተዳርጌያለሁ"* በማለት ለኮሚሽኑ ተናግረዋል።

## 4.5. በስደተኞች ላይ የደረሰ ሞት እና አካል ጉዳት

በጋምቤላ ክልል የተለያዩ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ በሚኖሩ የደቡብ ሱዳን ስደተኞች ላይ በመጠለያ ጣቢያ ውስጥ፣ እንዲሁም ከመጠለያ ጣቢያዎች ውጪ ለምግብ ፍለጋ እና ለተለያዩ ጉዳዮች ሲንቀሳቀሱ በታጠቁ ቡድኖች እና ግለሰቦች ቢያንስ 27 ሰዎች መገደላቸውን፣ በ12 ሰዎች ላይ ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት መድረሱን፣ እንዲሁም በንብረት ላይ ጉዳት መድረሱን ኮሚሽኑ ከስደተኞች ኮሚቴ፣ ከተጎጂዎች፣ ከተጎጂዎች ቤተሰቦች እና ከስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት ባሰባሰባቸው መረጃዎች እና ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ችሏል።

ሚያዝያ 12 ቀን 2015 ዓ.ም. ከቀኑ 11፡00 ሰዓት አካባቢ በጎግ ወረዳ፣ ፑኚዶ 1 የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ ልዩ ስሙ ማሌዢያ ተብሎ በሚጠራው ስፍራ የቀድሞውን የጋምቤላ ክልል ልዩ ኃይል መለዮ ልብስ የለበሱ የታጠቁ ቡድኖች እንጨት ለመልቀም የሄዱ 7 ሴት ስደተኞች ላይ ጥቃት ከከፈቱ በኋላ 6ቱ ሲያመልጡ አንዷን ይዘው በጩቤ ወግተው መግደላቸውን የሟች ቤተሰብ እና ሌሎች ምስክሮች አስረድተዋል።

ሰኔ 4 ቀን 2015 ዓ.ም. ከቀኑ 11፡00 ሰዓት አካባቢ ደቡብ ሱዳናዊ ስደተኛ በጎግ ወረዳ ከፑኝዶ ከተማ ወደ ፑኝዶ 2 የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ በብስክሌት እየተጓዘ በነበረበት ጊዜ የታጠቁ ሰዎች መንገድ ላይ ጠብቀው በጥይት ሁለት እግሩ ላይ ጉዳት አድርሰውበት ንብረቱን ወስደው ከአካባቢው መሰወራቸውን ተጎጂው ለኮሚሽኑ አስረድቷል። ኮሚሽኑ ይህንንም ክስተት የስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት ፑኝዶ 2 ጣቢያ አስተባባሪዎችን በማነጋገር እና የደረሰበትን ጉዳት በመመልከት አረጋግጧል።

ሰኔ 8 ቀን 2015 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ላይ ከተርፋም ወደ ጋምቤላ ከተማ በመጓዝ ላይ በነበረ በተለምዶ ባጃጅ እየተባለ በሚጠራው ባለ ሦስት እግር ተሽከርካሪ ላይ አቦል ከተማ አካባቢ የታጠቁ ቡድኖች በከፈቱት ተኩስ ሹፌሩን ጨምሮ 4 ሰዎች መገደላቸውን እና 2 ሰዎች መቁሰላቸውን ማወቅ ተችሏል።

ሰኔ 10 ቀን 2015 ዓ.ም. ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት ገደማ በጎግ ወረዳ፣ ፑኝዶ 1 የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ መንደር 13 ብሎክ “ኤ” ተብሎ በሚጠራው ስፍራ 7 ሆነው እራት እየተመገቡ በነበረበት ቦታ የእጅ ቦምብ ተወርውሮ 4 ስደተኞች ጉዳት የደረሰባቸው በመሆኑ ወደ ጋምቤላ ሆስፒታል ተወስደው ሕክምና እየተከታተሉ መሆኑን ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው የተጎጂዎች ቤተሰቦች፣ ሌሎች በመጠለያ ጣቢያው ከሚኖሩ ስደተኞች እና የስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት ፑኝዶ 1 ካምፕ ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

ሰኔ 18 ቀን 2015 ዓ.ም. ከምሽቱ 1፡00 ሰዓት አካባቢ በጎግ ወረዳ ፑኝዶ 2 የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ ውስጥ አንዲት ሴት ስደተኛ ላይ የታጠቁ ሰዎች ጉዳት ያደረሱባት ሲሆን፤ ሰኔ 25 ቀን 2015 ዓ.ም. ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት አካባቢ አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ደቡብ ሱዳናዊ ስደተኞች ላይ የታጠቁ ሰዎች በከፈቱት ተኩስ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ለኮሚሽኑ አስረድተዋል። ይህም ክስተት መድረሱን የስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት ፑኝዶ 2 ካምፕ አስተባባሪዎች ለኮሚሽኑ አረጋግጠዋል።

ሰኔ 26 ቀን 2015 ዓ.ም. ከምሽቱ 2፡15 ሰዓት አካባቢ የታጠቁ ቡድኖች ጉዊኘየል የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ ላይ በከፈቱት ጥቃት 1 ሰው መገደሉን እና 2 ሰዎች መቁሰላቸውን ታውቋል። እንዲሁም በሐምሌ 6 ቀን 2015 ዓ.ም. ከቀኑ 11፡00 ሰዓት አካባቢ ከተርፋም ወደ ጋምቤላ ከተማ በመጓዝ ላይ በነበረ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ (አውቶቡስ) ላይ በታጠቁ ቡድኖች በተከፈተ ጥቃት የ1 ስደተኛ ሕይወት ማለፉን እና 2 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ኮሚሽኑ ባሰባሰባቸው መረጃዎች ማወቅ ችሏል።

ሐምሌ 3 ቀን 2015 ዓ.ም. ከረፋዱ 5፡00 ሰዓት አካባቢ በጎግ ወረዳ፣ ፑኝዶ 1 የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ 5 ሰዎች እንጨት ለመልቀም ወደ ጫካ በሄዱበት ጊዜ ማንነታቸው ባልታወቁ የታጠቁ ቡድኖች በደረሰባቸው ጥቃት 1 ሰው የተገደለ ሲሆን ሌሎች 4 ሰዎች ሸሽተው አምልጠዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ በሐምሌ 13 ቀን 2015 ዓ.ም. ከሌሊቱ 4፡00 ሰዓት አካባቢ በጎግ ወረዳ፣ ፑኝዶ 1 የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ ብሎክ 1 ውስጥ 1 ስደተኛ ማንነታቸው ባልታወቀ የታጠቁ ቡድኖች በጥይት ተመትቶ መሞቱን ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው ምስክሮች እና የሟች ቤተሰቦች አስረድተዋል።

ሐምሌ 9 ቀን 2015 ዓ.ም. ከንጋቱ 11፡00 ሰዓት ገደማ የጀዊ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሁለት ስደተኞች ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች በጋምቤላ ወረዳ፣ ጀዊ ቀበሌ የአንድ ግለሰብ የእርሻ ልማት ውስጥ ተገድለው መገኘታቸውን፤ በተመሳሳይ ሁኔታ ነሐሴ 24 ቀን 2015

ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ገደማ በጋምቤላ ወረዳ፣ ጀዊ ቀበሌ የአንድ ግለሰብ የእርሻ ልማት ውስጥ ከሌላ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ ቤተሰብ ለመጠየቅ እንደመጣ የተነገረ አንድ ስደተኛ ባልታወቁ ሰዎች በጥይት ተገድሎ መገኘቱን ኮሚሽኑ በጀዊ መጠለያ ጣቢያው ውስጥ ከሚኖሩ ስደተኞች፣ የስደተኞች ተወካዮች እና ከጣቢያው አስተባባሪዎች ባሰባሰባቸው መረጃዎች ማወቅ ችሏል።

ሐምሌ 13 ቀን 2015 ዓ.ም. ከኩሌ፣ ተርኪዲና ጉዊኘየል የስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ይኖሩ የነበሩ 13 ሴት ስደተኞች ማኛንግ እና ባሮ ወንዝ አካባቢ በሚገኝ እርሻ ውስጥ በጥይት ተመትተው እና በጦር ተወግተው መገደላቸውን፤ በተመሳሳይ በዚሁ በሐምሌ ወር ውስጥ አንድ ሰው ከመጠለያ ጣቢያ ወጥቶ ወደ ፑልኮድ ቀበሌ አካባቢ በመሄድ ላይ እያለ መገደሉን ኮሚሽኑ የተጎጂ ቤተሰቦችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን፣ የስደተኞች ማዕከላዊ ኮሚቴዎችን እና የመንግሥት አካላትን በማነጋገር ማወቅ ችሏል።

ነሐሴ 23 ቀን 2015 ዓ.ም. ከምሽቱ 5፡00 ሰዓት አካባቢ በጎግ ወረዳ፣ ፑኝዶ 1 የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ አንድ ደቡብ ሱዳናዊት ስደተኛ በጥይት ተመትታ ጉዳት የደረሰባት መሆኑን ኮሚሽኑ የተጎጂ ቤተሰብን እና የመጠለያ ጣቢያውን አስተባባሪዎች በማነጋገር ማወቅ ችሏል።

ነሐሴ 25 ቀን 2015 ዓ.ም. ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት አካባቢ በጎግ ወረዳ ፑኝዶ 1 የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ ውችሩ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ 7 ስደተኞች ከሰል ለማክሰል ወደ ጫካ በሄዱበት ወቅት ሌሎች ስደተኞች በጦር መሣሪያ ተኩስ በመክፈታቸው ስድስቱ ሲያመልጡ አንድ ሕፃን ስደተኛ በጥይት እና በጦር የተገደለ መሆኑን ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው የሟች ቤተሰቦች እና የጎግ ወረዳ አስተዳደር አስረድተዋል።

መስከረም 10 ቀን 2016 ዓ.ም. ከሌሊቱ 7፡00 ሰዓት ገደማ ጉዊኘየል የስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውስጥ የታጠቁ ሰዎች በከፈቱት ጥቃት አንድ ሰው ላይ የአካል ጉዳት መድረሱን የተጎጂ ቤተሰብ እና የመጠለያ ጣቢያው አስተባባሪዎች ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

### 4.6. በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት እና ዘረፋ

በአብዛኛው ግጭት ወቅት ወደ ጋምቤላ ከተማ እና ወደ ወረዳዎች ለመጓዝ ከፍተኛ የደኅንነት ሥጋት የነበረ ሲሆን፣ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶብሶች፣ በስደተኞች ዙሪያ የሚሠሩ የተለያዩ ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች መጓጓዣዎች በፌዴራል ፖሊስ እና በሀገር መከላከያ ሰራዊት እጀባ ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል።

በሌላ በኩል ግጭቶች በተከሰቱባቸው አብዛኛው አካባቢዎች ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ነዋሪዎች ከቀያቸው ተፈናቅለው አጎራባች በሆኑ ቀበሌዎች ሰፍረው የነበረ ሲሆን፣ ይህ የምርመራ ሪፖርት በሚዘጋጅበት ወቅት ግን አብዛኞዎቹ ተፈናቃዮች ወደ መኖሪያ ስፍራቸው መመለሳቸውን የሚመለከታቸውን የመንግሥት አካላት በማነጋገር ለማወቅ ተችሏል።

በጋምቤላ ከተማ 04 ቀበሌ ብሔር ብሔረሰብ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ሰኔ 24 ቀን 2015 ዓ.ም. ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ገደማ ቁጥራቸው ከ200 በላይ የሚሆኑ በቡድን የተሰባሰቡና የታጠቁ ወጣቶች፣ የክልሉን መደበኛ ፖሊስ መለዮ የለበሱ እና የቀድሞውን የክልሉን ልዩ ኃይል መለዮ የለበሱ ታጣቂዎች ጭምር በሦስት አቅጣጫ ጥቃት በመክፈትና ወደ ሰፈሩ በመግባት 15 በሳር

የተሰሩ የመኖሪያ ቤቶችን ሙሉ በሙሉ አቃጥለው ያወደሙ መሆኑን ኮሚሽኑ በአካባቢው ባደረገው ምልከታ እንዲሁም ካነጋገራቸው የዐይን ምስክሮች ለማወቅ ችሏል፡፡

ሐምሌ 13 ቀን 2015 ዓ.ም. ከቀኑ 5፡00 ሰዓት አካባቢ በኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ፒኖ ቀበሌ የታጠቁ ቡድኖች እና የደቡብ ሱዳን ሚሊሻን መለዮ የለበሱ ታጣቂዎች በከፈቱት ጥቃት ቢያንስ 58 ቤቶች መቃጠላቸውን ኮሚሽኑ ተጎጂዎችን፣ ምስክሮችን እንዲሁም የቀበሌ አመራሮችን በማነጋገር እና በአካል ምልከታ በማድረግ ለማወቅ ችሏል፡፡ በተመሳሳይ ቀን በፑኩሙ ቀበሌ ውስጥ የታጠቁ ቡድኖች 35 የሳር ቤቶች አቃጥለው፤ ትምህርት ቤት እና የጤና ኬላ ውስጥ የነበሩትን ንብረቶች ዘርፈው መውሰዳቸውን ኮሚሽኑ ካነጋገራቸው ምስክሮች ለማወቅ ችሏል፡፡

ሐምሌ 18 ቀን 2015 ዓ.ም. ከሌሊቱ 10፡00 ሰዓት በኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ ሌር ቀበሌ የታጠቁ ቡድኖች፣ የክልሉን መደበኛ ፖሊስ መለዮ የለበሱ እና የቀድሞውን የክልሉን ልዩ ኃይል የደንብ ልብስ የለበሱ ታጣቂዎች በከፈቱት ጥቃት ቢያንስ 180 የሣር ቤቶች፣ እና ፍየሎችን ጨምሮ 260 የሚሆኑ የቀንድ ከብቶች ማቃጠላቸውን ምስክሮች፣ የአካባቢው ነዋሪዎች እና የቀበሌ አመራሮች ገልጸዋል፡፡

በዚሁ ዕለት እና ተመሳሳይ ሰዓት ሐምሌ 18 ቀን 2015 ዓ.ም. ከሌሊቱ 10፡00 ሰዓት አካባቢ በኢታንግ ልዩ ወረዳ ፑልዴንግ ቀበሌ የታጠቁ ቡድኖች፣ የክልሉን መደበኛ ፖሊስ መለዮ የለበሱ እና የቀድሞውን የክልሉን ልዩ ኃይል የደንብ ልብስ የለበሱ ታጣቂዎች በከፈቱት ጥቃት ቢያንስ 170 የሣር ቤቶችን፣ ፍየሎችን ጨምሮ ከ100 ያላነሱ የቀንድ ከብቶችን አቃጥለዋል፤ በተጨማሪም በአካባቢው የሚገኝ ትምህርት ቤት ንብረቶችን እና ከ90 ያላነሱ የቀንድ ከብቶችን ዘርፈው መውሰዳቸውን ለማወቅ ችሏል፡፡

መስከረም 10 ቀን 2016 ዓ.ም. ከሌሊቱ 7፡00 ሰዓት ገደማ በኢታንግ ልዩ ወረዳ ጉዊኘየል የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ ላይ በተፈጸመ ጥቃት 2 የጎጆ ቤቶች እና 5 ፍየሎች ተቃጥለዋል፡፡

## 5. የመንግሥት አካላት ምላሽ

ከግንቦት ወር 2015 ዓ.ም. ጀምሮ በኢታንግ ልዩ ወረዳ የተለያዩ ቀበሌዎች ጨምሮ ወደ ክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች በተስፋፋው የጸጥታ መደፍረስ፣ ጥቃቶች እና ግጭቶች የተነሳ በሰው ሕይወት፣ አካልና ንብረት ላይ የደረሱትን ጉዳቶች በተመለከተ ኮሚሽኑ በክልል፣ በዞን እና በወረዳ ደረጃ የሚገኙ የተለያዩ የክልሉን የመንግሥት አካላትን፣ የፌዴራል የመንግሥት ተቋማትን እና የሆስፒታል አስተዳደሮችን በማነጋገር መረጃዎችን እና ምላሾችን ተቀብሏል፡፡

የኢታንግ ልዩ ወረዳ አስተዳደር በግጭቱ እጃቸው አለበት ተብለው የተጠረጠሩ 3 አመራሮች በሕግ ቁጥጥር ሥር ውለው ምርመራ እየተጣራ እንደሆነና ማኅበረሰቡን ወደነበረበት የቀድሞ ሁኔታ ለመመለስ የዕርቅ እና ሰላም መድረኮች እና ውይይቶች ተዘጋጅተው እንደነበር ለኮሚሽኑ ገልጿል፡፡ የኢታንግ ልዩ ወረዳ ፖሊስ ጽሕፈት ቤት ከግጭቱ ጋር በተያያዘ ተጠርጥረው የታሰሩ የወረዳው አመራሮች መኖራቸውንም ለኮሚሽኑ አስረድቷል፡፡

የአኝዋ ብሔረሰብ ዞን ሰላም እና ጸጥታ ጉዳዮች መምሪያ ከተፈጠሩት የጸጥታ ችግሮች በኋላ በመንግሥት በኩል ሰፊ ግምገማዎች ተደርገው በጉዳዩ ላይ ተሳትፎ አላቸው ተብለው የተጠረጠሩ አመራሮች ከሥልጣን እንዲነሱ እና እንደ ወንጀል ተሳትፏቸው በሕግ እንዲጠየቁ የማድረግ ሥራዎች መከናወን በመጀመራቸው በአሁኑ ጊዜ አንጻራዊ ሰላም መፈጠሩን ገልጸው፣ *"በሕዝብ*

*ሳይሆን በአመራሮች መካከል ባሉ አለመግባባቶች እና ከሕዝብ ይልቅ የራስን ፍላጎት የማስቀደም አካሄዶች በመኖራቸው የተነሳ የተፈጠረ ችግር መሆኑን”* እንደሚያምኑ አስረድተዋል፡፡

የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር በጸጥታ ችግሮች የተነሳ በሰው ሕይወት እና ንብረት ላይ ጉዳት መድረሱን ነገር ግን አዲስ አመራር በመሆናቸው ዝርዝር መረጃዎች እንደሌሏቸው ገልጸዋል፡፡ አስተዳደሩ አክለው ሲገልጹም ጋምቤላ ውስጥ የሚከሰቱት አብዛኞቹ የማኅበረሰብ ግጭቶች መነሻ ምክንያታቸው የመሬት፣ የሥልጣን እና የስደተኞች ጉዳይ ቢሆንም ማኅበረሰቡ አብሮ የኖረ እና ግጭት የማይፈልግ መሆኑን፣ አለመግባባቶች የሚስተዋሉት በተማሩ እና የተለያየ የሥልጣን/የኃላፊነት ቦታ ይዘው በሚገኙ ሰዎች መካከል መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የተፈጠረውን የጸጥታ ችግር ለመፍታት እና ወደፊት ሊፈጠሩ የሚችሉ ግጭቶችን ለመከላከል ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት ልዩነቶችን በውይይት መፍታት እንደሚያስፈልግ ለኮሚሽኑ አስረድተዋል፡፡ የጋምቤላ ከተማ የ01 ቀበሌ አስተዳደር ኃላፊዎች በቀበሌው ውስጥ ተከስቶ የነበረውን የጸጥታ ችግር አስመልክቶ በተደረገ ግምገማ መሠረት ነባር የቀበሌው አስተዳደር ኃላፊዎች ከኃላፊነታቸው ተነስተው አዲስ ኃላፊዎች በመተካታቸው ዝርዝር መረጃዎች የሌሏቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ የጋምቤላ ከተማ የ04 ቀበሌ አስተዳደር ኃላፊዎች የጸጥታ ችግሩ በተከሰተበት ጊዜ የነበሩት የቀበሌ አስተዳደሩ ኃላፊዎች የጸጥታ ችግሩን ተከትሎ በተደረገ ግምገማ ከኃላፊነት ተነስተው በምትኩ አዲስ አመራር መመረጡን ገልጸዋል፡፡

በተለይም ከመስከረም ወር 2016 ዓ.ም. ወዲህ እስከ ጥር ወር 2016 ዓ.ም. በተከሰቱ ግጭቶች ላይ የጋምቤላ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን እና የክልሉ ሰላም እና ጸጥታ ጉዳዮች ቢሮ በክልሉ በተለያዩ ቦታዎች ላይ በደረሱ ጥቃቶች ላይ የተጠረጠሩ ሰዎችን ተከታትሎ ወደ ሕግ የማቅረብ ሥራዎች ከማከናወን በተጨማሪ ችግር በተከሰተባቸው ቦታዎች የአካባቢውን ባህል እና ወግ መሠረተ ያደረገ የማኅበረሰብ ውይይት እና ዕርቅ እየተካሄደ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ ከእነዚህ እርምጃዎች በተጨማሪ በተለያየ ጊዜያት የጸጥታ ችግሮች የሚከሰትባቸውን ቦታዎች በመለየት በሀገር መከላከያ ሰራዊት እንዲጠበቅ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የጋምቤላ ክልል መንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤትም በመንግሥት በኩል ሰፊ የውይይት መድረኮች በማካሄድ እና ግምገማዎች በማድረግ በግጭቱ ተሳታፊ እንደነበሩ የተጠረጠሩ የወረዳ አመራሮች ከኃላፊነታቸው ተነስተው በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራዎች በስፋት እየተከናወኑ መሆኑን ለኮሚሽኑ አስረድተዋል፡፡

የፌዴራል ፖሊስ የወንጀል መከላከል የደቡብ ምዕራብ ሬጅመንት 2 ጋምቤላ ጽሕፈት ቤት በበኩሉ በተፈጠረው የጸጥታ ችግር ተሳትፈዋል ተብለው ተጠርጥረው በቁጥጥር ሥር በዋሉ የአስተዳደር አመራሮች ላይ የወንጀል ምርመራ እየተደረገ እንደሆነ ገልጿል፡፡

የስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት ጋምቤላ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤትም በሰዎች ግድያ፣ የአካል ጉዳት እና ዝርፊያ በመሳሰሉ ድርጊቶች ላይ የተሳተፉ ተጠርጣሪ ስደተኞችን በመለየት እና ምርመራ በማከናወን ወደ ሕግ እንዲቀርቡ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## 6. ምክረ ሐሳቦች

- የፌዴራል እና የክልሉ መንግሥታት በጋራ በመሆን በግጭቱ ላይ በቀጥታ በተሳተፉ የአስተዳደር አካላት፣ የክልሉ መንግሥት የጸጥታ ኃይል አባላት፣ የታጠቁ ቡድኖች እና ግለሰቦች ላይ ተገቢውን የወንጀል ምርመራ በማድረግ ተጠያቂነትን እንዲያረጋግጡ፤
- የጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በክልሉ የሚገኙትን የጸጥታ መዋቅሮች በመፈተሽ ብቁ፣ ሚዛናዊ እና ግጭቶችን ከወገንተኝነት በጸዳ መልኩ ለማረጋጋት የሚያስችል ብቃት ያለው የጸጥታ ተቋም እንዲገነባ፤
- የጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከሌሎች አጋዥ ድርጅቶች ጋር በትብብር እና በጥምረት በመሥራት በግጭቱ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ተገቢውን ካሳ እንዲያገኙ እንዲያደርግ፤
- የስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት ከተቀባይ ማኅበረሰብ፣ ከክልል እና ከፌዴራል መንግሥት እንዲሁም ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመሆን በስደተኞች እና በተቀባይ ማኅበረሰብ መካከል ያሉ አለመግባባቶች እና ያለመግባባት ምክንያቶች በዘላቂነት የሚፈቱበትን መንገድ ለመፍጠር ጥረቶች እንዲያደርግ፤
- ወደፊት ተመሳሳይ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች እንዳይከሰቱ ለመከላከል አስፈላጊ የሆኑ አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ እና የተጀመሩ የመልሶ ማቋቋም፣ የማኅበረሰብ ውይይቶች፣ የዕርቅ እና የሰላም መድረኮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ኮሚሽኑ ያሳስባል።